# ማንም አይፈራህም ማንም

ሸባባው

እኔ ብቻ ልናገር ማንም አይናገር እኔ ብቻ ላድርግ እኔ ብቻ በነፃነት ልኑር እኔ ያልኩትን ብቻ ስሙ ሙሉ የአገሪቱ ህዝብ ዝም ይበል የሚል የዲሞክራሲ አስተሳሰቡ ያረጀ ነው ሰውየው።

በቃ የሰውየው ፈሪነት ብቻ አይደለም ጥላውንም የሚያምን አይመስልም። በሀሳብ የሞገቱ ይሄ መንገድ ልክ አይደለም ይስተካከል ያሉ በቃ በምንም መንገድ ይሁን በተለይ የአማራ ተወላጆች ላይ ሰውየው ማሰር ማንገላታት የሚያስቆመው መስሎታል።

አብረውት የሰሩት ሰወች በሀሳብ ካልተስማሙ በወታደር ይወራቸዋል ቤታቸውን ይፈትሻል ያስራቸዋል። ከዚህ ውጭ ሰውየው አያውቅም የዘመናዊ መሪ አስተሳሰቡ እያየነው በኖ ጭራሽ ወደ አስራ ሰባተኛው ክፍለዘመን እሳቤ ተጠልፎዋል።

ስለዚህ እኔ ብቻ ልናገር ዝም በሉ ሙብት የላችሁም እኔ ገዣችሁ ነኝ እኔ ስናገር አሜን በሉ አጨብጭቡ የሚል ሁዋላቀር አስተሳሰብ ተሸክሞዋል።

በማሰር በመግደል የትኛውንም ሰው ማስፈራራት አይቻልም በተለይም በዚህኛው ዘመን። ይህን ሁዋላቀር መንገድ የተከተሉ የየትኛውም አገር መሪወች ሁሉ ተንቀዋል።

አብይ አህመድን የሚፈራ ካለ እርግጠኛ ነኝ እሱ የተመታ መንፈስ ያለው ሰው ብቻ ነው። ለምን ሙሉ ጦሩን ከፊት አይደቅንም በጭራሽ እሱን የሚፈራ አይፈጠርም።

ዘመናዊ መሪ በምርጥ ዘመናዊ ትውልድ ለዋጭ ሀሳብ ይከበራል ይደነቃል እንደነ ሳውዲ አረብያ ከበረሀ አንስተው በጥበብ የምድር ውብ አገርን የፈጠሩ እንደነ ሲንጋፖር ሩዋንዳ የመሳሰሉ አገራት ጥበበኛ መሪወች አይነት አስተሳሰብን የያዘ መሪ ዘመን ተሻጋሪ በትውልድ ላይ አሻራን ያስርፋል።

አብይ አህመድ ፍርሀቱ ብቻ አይደለም እንደ ጎረቤት ኬንያ መሪ አይነት የሰለጠነ ሀሳብ ቢነሳበት ሰውየው ዱዳ መግባቱ ነው። የኬንያው መሪ የአገሩ ዜጎች የፈለጉትን ሀሳብ እንዲያንሸራሽሩ ፈቀደ ከዜጎቹ ጋር ፊትለፊት መወያየትን መከራከርን መረጠ። በሀሳብ የሚተቹትን ይበልጥ አቀረባቸው እንኳን ሊያስር በፍርሀት ቀርቶ ኑ ተቹኝ ስህተቴን ንገሩኝ ብሎ ዜጎቹን ጋበዘ።

የኢትዮጵያው መሪ በህዝብ ላይ የከፈትከው ጦርነት ልክ አይደለም እስከመቸ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጩ አገር ትመራ ሰለቸን ሌላ መንገድ ካለ ይቀየር የአገሪቱ ጦር እንደ ተራ መጫወቻ ሆነ ድንበር እንደ ወንዶቹ መጠበቅ ሲገባው የአገሩን ዜጎች በመግደል የተዋረደ ርምጥምጥ ሆነ ብለው ሀሳብ ይሰጡታል ሰውየው ድንብርብሩ ወቶ ቤታቸውን ፈተሸ ተብሎ ሰማን።

ዮሀንስ ቧያሌው በግልጽ ይህ እንደሚመጣ ለጠቅላዩ ቅድሚያ ነግሮት ነበር ጠቅላዩ ግን ስልትም የመምራት ብቃትም ስለሌለው አሰረው ይሄ ለጠቅላዩ ትልቅ ውርደት መሆኑ አልገባውም።

ዮሀንስ ቧያሌው ያለው ሁሉ ሆነ የጠቅላዩ ቅሌት አገሪቱን ማጥ ከተታት ። ጠቅላዩ የሰለጠነ ቢሆን ኖሮ ቁጭ ብለን እንምከር በሰለጠነ መንገድ እንፍታው አንድ ንብረት መውደም አንድ ዜጋ መሞት ለአገር ጉዳት ነው አላለም በሀሳብ የበለጡትን እስር ቤት ይልካል።

ምን እየተፈጠረ መጣ ሰውየውን የሚፈራም የሚያከብርም ሰው እየጠፋ መጣ የአምባ ገነን እና ሁዋላቀር መሪወች መጨረሻ እንዲህ ነው መግደል ማሰር ወዘተ ዜጎችን ይበልጥ ቂጣ ውስጥ ጥሎ ሺ ጦር ብታንጎማልል መስሚያው ጥጥ ይሆንና ሰው ያስነቅልሀል

ቧያሌውን በማሰር የምታቆመው አንዳች ትግል የለም አንድም ተመልከት ወጣቱን ነፍጥ እያነሳ ምሽግ ገብቶዋል አንተን መቸም የሚፈራህ አይኖርም መቸም።

16/05/2023